IslamHouse.com
مركز أصول
Osoul Center
www.osoulcenter.com



# صفة صلاة النبي ﷺ

# የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አሰጋገድ ስርዓት

Amharic
አማርኛ
أمهري

አዘጋጅ፡
አብዱልዐዚዝ ቢን አብደላህ ቢን ባዝ
ተርጓሚ፡
ጋሊ አባቦር አባጉማ
እርማት፡
ሼኽ ጀማል ሙሀመድ

# صفـــة صـــلاة النبـــــي ﷺ

تأليف

عبدالعزيز بن عبدالله بن باز

ترجمة

الداعية غالي أبا بور

مراجعة

الداعية جمال محمد أحمد

Amharic
አማርኛ
أمهري

ⓒ **جمعية الدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالربوة، ١٤٤٢هـ**

**فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر**

مركز أصول

صفة صلاة النبي صلى الله عليه وسلم – اللغة الأمهرية. / مركز أصول - ط١.- الرياض، ١٤٤٢هـ

٢٨ ص، ١٢ سم x ١٦,٥ سم

ردمك : ٩٧٨-٦٠٣-٨٣٢٣-٣٣-٥

١- الصلاة ٢- السيرة النبوية أ. العنوان

**ديوي ٢٥٢,٢ ١٤٤٢/٢٧٠٠**

**رقم الايداع: ١٤٤٢/٢٧٠٠**

**ردمك : ٩٧٨-٦٠٣-٨٣٢٣-٣٣-٥**

مركز أصول
Osoul Center
www.osoulcenter.com

This book is the property of the Osoul Center. Permission is granted for it to be stored, transmitted, and published in any print, electronic, or other format - as long as the Osoul Center is clearly mentioned on all editions, no changes are made without the express permission of the Osoul Center, and a high level of quality is maintained.

+966 11 445 4900

+966 11 497 0126

P.O.BOX 29465 Riyadh 11457

osoul@rabwah.sa

www.osoulcenter.com

بسم الله الرحمن الرحيم

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ
እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው



## መቅድም

ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላም በነቢዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን፡፡ በመቀጠል ይህችህ አጠር ያለች ጽሑፍ የነቢዩ (ሰዐወ) ሰላት ስረዓት ለማብራራት የተጻፈች ናት፡፡ እሷን ያየ ሙስሊም ሁሉ በሰላቱ ዉስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለመከተል እንድተጋ አቀረብኩለት፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋልና "እኔ ሲሰግድ እንዳያችሁኝ ስገዱ፡፡" ቡኻሪ ዘግበውታል፡፡ ማብራርያውም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1 ዉዱእን ማዳረስ፡- እሱም አላህ (ሱወ) በቀጣዩ አንቀፅ እንዳዘዘው ዉዱእ በማድረግ ይሆናል፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا قُمۡتُمۡ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ فَٱغۡسِلُواْ وُجُوهَكُمۡ وَأَيۡدِيَكُمۡ إِلَى ٱلۡمَرَافِقِ وَٱمۡسَحُواْ بِرُءُوسِكُمۡ وَأَرۡجُلَكُمۡ إِلَى ٱلۡكَعۡبَيۡنِ﴾ [المائدة: ٦]

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሰላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ፡፡ ራሶቻችሁንም (በውሃ) አብሱ፡፡ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)፡፡" አልማኢዳ፡6

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ "አላህ ማንኛውንም ሰላት ያለ ጠሃራ (ዉዱእ) አይቀበልም፡፡"

የዉዱእ አደራረግ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ዉዱን በልቡ ብቻ ይነይታል፣ በምላሱ አይናገረውም፡፡ ምክንያቱም

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዉዱም ሆነ በሰላት ዉስጥ ንያን በአንደበት አልተናገሩምና፡፡ አላህም በልብ ዉስጥ ያለውን ሲለሚያውቅ መናገሩ አያስፈልግም፡፡

ቀጥሎ "ብስምላህ" (በአላህ ስም) ይላል፡፡

1. በመቀጠል መዳፉን ሦስት ጊዜ ያጥባል፡፡
2. የሚቀጥለው ደግሞ ሦስት ጊዜ አፍን መጉመጥመጥና በአፍንጫው ዉሃን ስቦ በግራ እጁ መልሶ ማስወጣት ይሆናል፡፡
3. በመቀጠል ፊቱን ሦስት ጊዜ ያጥባል፡፡ ፊት የሚባለው በጎን ከጆሮ እስከ ጆሮ ሲሆን ከላይ ወደታች ደግሞ ከጭንቅላት ፀጉር ማብቀያ እስከ አገጭ ስር ይሆናል፡፡
4. ቀጥሎም ሁለት እጆቹን ከጣት ጫፍ እስከ ክርኖቹ ድረስ ሶስት ጊዜ ያጥባል፡፡ በቀኝ ይጀምርና ግራን ያስከትላል፡፡
5. በመቀጠል ፀጉሩን አንድ ጊዜ ያብሳል፡፡ እጆቹን በማርጠብ ከግንባሩ ጀምሮ እስከ ማጅራቱ ያብስና ወደ ጀመረበት ይመለሳል፡፡
6. በመቀጠል ጆሮዎቹን አንድ ጊዜ ያብሳቸዋል፡፡ አመልካች ጣቶቹን ጆሮዎቹ ዉስጥ በማስገባት በአውራ ጣቶቹ የጆሮዎቹን ጀርባ ያብሳል፡፡
7. ቀጥሎ ሁለት እግሮቹን ከጣት ጫፎች ጀምሮ ቁርጭምጭሚቶቹን ጨምሮ ያጥባቸዋል፡፡ በቀኝ ጀምሮ ግራውን ያስከትላል፡፡
8. የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- "ከናንተ መካከል

አንድም ሰው ዉዱን አድርጎ፣ ዉዱውንም አሟልቶ አድርጎና ቀጥሎም "ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ እንደ ሌለ እመሰክራለው፤ እርሱ አንድ ነው አጋር የለውም፡፡ ሙሐመድም ባርያውና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለው" ብሎ አይቀርም ስምንቱም የጀነት በሮች ብከፈቱለት እንጅ፡፡ ከሷ መካከል በፈለጋት ይገባል፡፡" ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

## 2 ወደ ቅብላ መዞር

ማንኛውም ሰጋጅ ዬትም ቢሆን በልቡ የሚስግደዉ ሰላትን እየነየተ በሙሉ ሰዉነቱ ወደ ቅብላ (ከዕባ) መዞር አለበት፡፡ ንያን በአንደበቱ አይናገርም፡፡ምክንያቱምበአንደበትመናገርአልተፈቀደምና፡፡ይልቁንስ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ሰሓባዎች ንያን በአንደበታቸው ሲላልተናገሩ ቢድዓ ትሆናለች፡፡ ኢማም ወይም ብቻውን የሚሰግድ ሰው ከሆነ ወደሱ የሚሰግድበትን ነገር ሲትርን (ከለላ ነገር) ፊት ለፊቱ ላይ ያደርጋል፡፡ ወደ ቅብላ መዞር የሰላት መስፈርት ነው፤ ግን የተወሰኑ ሰላቶች ዉስጥ መስፈርት መሆኑ ይቀራል፡፡ እነሱም በፍቅህ ኪታቦች ዉስጥ ተዘርዝረዋል፡፡[1]

ተክቢረት አልኢሕራም ማድረግ፣ የተክቢራ ጊዜ እጅን ማንሳትና ሁለት እጆችን ደረት ላይ ማስቀመጥ

## 3 በዐይኑ የሱጁድ ቦታ እያየ ተክቢረት አልኢሕራም (ወደ ሰላት መግቢያ ተክቢራን) "አላሁ አክበር" ብሎ ያደርጋል፡፡

1 ለምሳሌ ሰላት አልኸውፍ፣ በመጓጓዣ ላይ የሚሰገድ ሱና ሰላትና የመሳሰሉት፡፡

4 ተክቢራ በሚያደርግ ጊዜ እጆቹን እስከ ትከሻው ወይም እስከ ጆሮዎቹ ድረስ ከፍ ያደርጋል፡፡

5 የቀኝ እጁን መዳፍ በግራ እጁ ላይ አስቀምጦ በደረቱ ላይ ያደርጋል፡፡ ይህ ድርጊት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተረጋግጧልና፡፡

6 በመቀጠል የሰላት መክፈቻ ዱዓእ ያደርጋል፡፡ እሱም የሚከተለው ይሆናል፡-

«اللهم باعد بيني وبين خطاياي كما باعدت بين المشرق والمغرب، اللهم نقني من خطاياي كما ينقى الثوب الأبيض من الدنس، اللهم اغسلني من خطاياي بالماء والثلج والبرد»

“አልላሁምመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጣያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወል መግሪቢ፡፡ አልላሁምመ ነቅቂኒ ሚን ኸጣያየ ከማ ዩነቅቃ አሥ- ሠውቡ-ል-አብየዱ ሚነድ-ደነሲ፡፡ አልላሁምመ ኢግሲልኒ ሚን ኸጣያየ ቢልማኢ ወሥ-ሠልጂ ወልበረዲ፡፡”

ትርጉሙ፡- ‹‹አላህ ሆይ! በምስራቅና ምዕራብ መካከል ያራራቅከውን ያህል በኔና በኃጢአቴ መካከልም አራርቅ፡፡ አላህ ሆይ! ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚጸዳው ሁሉ እኔንም ከኃጢአቴ አጽዳኝ፡፡ አላህ ሆይ! ከኃጢአቴ በውሃ፣ በቀዝቃዛ ውሃ እና በበረዶ እጠበኝ፡፡››

«سبحانك اللهم وبحمدك وتبارك اسمك وتعالى جدك ولا إله غيرك»

“ሱብሓነከ-ልላሁመ፥ ወቢሐምዲከ፥ ወተባረከ ኢስሙከ፥ ወተዓላ ጀድዱከ፥ ወላ ኢላሀ ገይሩከ”

ትርጉም፡- «አላህ ሆይ! አንተን ከማመስገን ጋር አጠረሃለውኝ፡፡ ስምህም ተባረከ፡፡ ክብርህም ከፍ አለ፡፡ ካንተ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም፡፡»

ከዚህ ሌላ ያለውን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መምጣታቸው የተረጋገጠውን የመክፈቻ ዱዓእ ቢያደርግም ችግር የለውም፡፡ በላጩ እነዚህን ዱዓ ቀያይሮ በተለያየ ጊዜ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መልክ ሙሉ በሙሉ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) መከተል ይቻላል፡፡ ቀጥሎ እንዲህ ይላል፡-

أعوذ بالله من الشيطان الرجيم، بسم الله الرحمن الرحيم،

ከአላህ እዝነት ከተባረረ ሸይጣን በአላህ (ሱወ) እጠበቃለውኝ፡፡ በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው፡፡

በመቀጠል ሱረት አልፋቲሓን ይቀራል፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ብለዋል፡- “ፋቲሐን ያልቀራ ሰው ሰላት የለውም፡፡” ቀጥሎ “ኣሚን” ይላል፡፡ ከፍ ተድርገው በሚቀሩ ሰላቶች ውስጥ ድምፁን ከፍ ያደርጋል፤ ዝቅ በሚደረገው ውስጥም ዝቅ ያደርጋል፡፡ በመቀጠል ከቁርኣን የገራለትን ይቀራል፡፡ የሚመረጠው በዙህር፣ ዐስርና መግሪብ ሰላት ላይ መካከለኛ ርዝመት ያላቸውን ሱራዎች መቅራት ሲሆን ሱብሒ ሰላት ላይ ደግሞ ረዣዥሞቹን ይቀራል፡፡ መግርብ ላይ ደግሞ አንድ አንዴ ከረዣዥሞቹ ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ አጫጭሮችን ይቀራል፡፡ ምክንያቱም በዚህ መልኩ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ተዘግቧልና፡፡



7 ተክቢራ እያለ እጆቹን እስከ ትከሻው ወይም ጆሮዎቹ ድረስ ከፍ እያደረገ ሩኩዕ ይወርዳል (ያጎነብሳል)፡፡ ጭንቅላቱን በወገቡ ልክ ያደርጋል፡፡ ጣቶቹን ለያይቶ ጉልበቱ ላይ ያደርጋል፡፡ ሱጁዱ ዉስጥ ተረጋግቶ ቀጣዩን ዚክር ያደርጋል፡-

‹ሱብሓነ ረብየል ዐዚም›

ትርጉሙም፡ ታላቁ ጌታዬ ላንተ ከማይገባህ ሁሉ ጥራት ይገባህ

የሚወደደው ይህን ዚክር ሶስትና ከዚያ በላይ መደጋገም ነው፡፡ ከሱ ጋርም ቀጣዩን ዚክር ቢጨምር ይወደዳል፡-

‹‹ሱብሓነከልላሁመ ረበና ወቢሐምዲከ፣ አሏሁምመ ኢግፊር ሊ››

ትርጉም፡- ‹‹አላህ ሆይ! አንተን ከማመስገን ጋር አጠራሃለው፡፡ አላህ ሆይ፣ ማረኝ››

8 እጆቹን እስከ ትከሻው ወይም ጆሮዎቹ ድረስ ከፍ እያደረገ ከሩኩዕ ይነሳል፡፡ ኢማም ወይም ብቻውን የሚሰግድ ሰው ከሆነ ቀጣዩን ዚክር ይላል፡-

ሰሚዐላሁ ሊመን ሐሚደህ

ትርጉም፡ አላህ እሱን ያመሰገነ ሰውን ይሰማል፡፡

ሁሉም ሰጋጅ ‹ረበና ወለከል ሐምዱ› (ጌታችን ሆይ! ምስጋና ያንተ ነው) ማለት ግዴታ ነው፡፡ ቆመው ባሉበት የሚቀጥለውን ዚክር ቢያደርጉ ይመረጣል፡-

«ربنا ولك الحمد حمدًا كثيرًا طيبا مباركًا فيه ملء السماوات وملء الأرض وملء ما بينهما وملء ما شئت من شيء بعد أهل الثناء والمجد أحق ما قال العبد وكلنا لك عبد، اللهم لا مانع لما أعطيت ولا معطي لما منعت ولا ينفع ذا الجد منك الجد»

«አልላሁምመ ረበና ወለከል ሐምዱ፥ ሚልአስ-ሰማዋቲ ወሚልአ-ል-አርዲ፥ ወሚልአ ማ ሺእተ ሚን ሸይኢን በዕዱ። አህለሥ-ሠናኢ ወል-መጅዲ፣ አሐቅቁ ማ ቃለል ዐብዱ ወኩልሉና ለከ ዐብዱን፥ አልላሁምመ ላ ማኒዐ ሊማ አዕጠይተ፥ ወላ ሙዕጢየ ሊማ መነዕተ፥ ወላ የንፈዑ ዘል ጀድዲ ሚንከ-ል-ጀድዱ።”

“ጌታችን ሆይ! ምስጋና የሚገባው ላንተ ነው። መልካም፣ ብዙ፣ የተባረከ ምስጋናን አመሰግንሃለው። በሰማያት ሙሉ በመሬት ሙሉ፣ እንዲሁም አንተ በፈለግከው ነገር ሁሉ የሚሞላ (ምስጋናን አመሰግንሃለው)። የውዳሴና የክብር ባለቤት የሆንክ ጌታ ሆይ! ሁላችንም ላንተ ባሪያዎች ነንና፣ ባሪያህ ካለ ሁሉ እወነተኛው ቃል “አላህ ሆይ! የሰጠኸውን የሚነሳ፥ የከለከልከውን የሚሰጥ የለም። ባለ ንብረትን ካንተ ቅጣት ንብረቱ ቅንጣት አይፈይደውም” የሚል ነው።

በዚህ ጊዜም ከሩኩዕ በፊት እንዳደረገው እጆቹን በደረቱ ላይ ማስቀመጥ ይወደዳል። ምክንያቱም ይህንን የሚያመላክት ሐዲስ ከዋእል ቢን ሑጅር እና ሰህል ቢን ሰዕድ (ረዐ) ተዘግበዋልና።

9

ተክቢራ እያለ ሱጁድ ይወርዳል። ከተመቸው ከእጆቹ በፊት ጉልበቶቹን መሬት ላይ ያስቀምጣል። ካልተመቸው ደግሞ እጆቹን

ከጉልበቶቹ ያስቀድማል፡፡ የእግሮቹና የእጆቹን ጣቶች ወደ ቅብላ ያዞራል፡፡ የእጆቹን ጣቶች ገጣጥሞ በመዘርጋት ሱጁድ ያደርጋል፡፡ ሱጁድ በሰባት አካላት ይደረጋል፡- ግንባር ከአፍንጫ ጋር፣ ሁለቱ እጆች፣ ሁለቱ ጉልበቶች እና የእግር ጣቶች ዉስጠኛው ክፍል ናቸው፡፡ ሱጁድ ዉስጥ ቀጣዩን ዚክር ይላል፡-

‹ሱብሓነ ረብየል አዕላ›

ትርጉም፡- የላቅክ ጌታዬ ላንተ ከማይገባህ ሁሉ ጥራት ይገባህ፡፡

ይህን ዚክር ሶስትና ከዚያ በላይ ብያደርግ ይመረጣል፡፡ በተጨማሪ ቀጣዩን ዚክር ብያደርግ ይወደዳል፡-

«ሱብሓነከልላሁመ ረበና ወቢሐምዲከ፣ አሏሁምመ ኢግፊር ሊ»

ትርጉም፡- «አላህ ሆይ! ከምስጋናህ ጋር አጠረሃለው፡፡ አላህ ሆይ፣ ማረኝ»

ሱጁድ ዉስጥ ዱዓእን ማብዛት ይወደዳል፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- “ሩኩዕ ላይ አላህን አልቁት፡፡ ሱጁድ ላይ ደግሞ ዱዓን አብዙ፡፡ ተቀባይነት ልታገኙ ተስፋ አለውና፡፡” የዱንያና የአኺራ ጥሩ ነገርን አላህን ይለምናል፡፡ ሰላቱ ዋጅብም ሆነ ሱና ቢሆን ችግር የለውም፡፡ የእጆቹን ጡንቻዎች ከጎኖቹ፣ ሆዱን ከጭኖቹ እና ጭኖቹን ከባቶቹ ያራርቃል፡፡ ክንዶቹንም ከመሬት ላይ ያነሳል፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- “ሱጁድ ዉስጥ ተስተካከሉ፤ አንዳችሁ ዉሻ እጆቹን እንደ ሚዘረጋ አትዘርጉ፡፡”

10

ተክቢራ እያለ ከሱጁዱ ይነሳል፡፡ ግራ እግሩን ዘርግቶ



ይቀመጥበታል፡፡ የቀኝ እግሩን ጣት ተክሎ ያቆማል፡፡ ሁለት እጆቹን በጭኖቹ ወይም ጉልበቶቹ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ቀጣዩንም ይላል፡-

“አሏሁምመ ኢግፊር ሊ፣ ወርሐምኒ፣ ወህዲኒ፣ ወርዙቅኒ፣ ወዓፊኒ፣ ወጅቡርኒ፡፡”

ትርጉሙም፡- “አላህ ሆይ! ማረኝ፡፡ እዘንልኝም፡፡ ቅኑን ጎዳናም ምራኝ፡፡ ሲሳይም ለግሰኝ፡፡ ጤነኛም አድርገኝ፡፡ ጉድለቴንም ጠግንልኝ፡፡” በዚህ ጊዜ ተረጋግቶ ይቀመጣል፡፡

11 ተክቢራ ብሎ ሱጁድ ያደርጋል፡፡ በመጀመርያው ሱጁድ ላይ ያደረገውን ይደግማል፡፡

12 አሁንም ተክቢራ ብሎ ይነሳል፡፡ አጠር ያለች ጊዜ በሁለት ሱጁዶች መሀከል ያለችዋን ያክል ቆይታ ይቀመጣል፡፡ እሷም “ጀልሰት አል-ኢስትራሓ” ትባላለች፡፡ እሷ ሱና ናት፣ ትወደዳለችም፡፡ ብተዋትም ችግር የለውም፡፡ በሷ ዉስጥ ዱዓም ሆነ ዚክር የለም፡፡ ቀጥሎም ከተመቸው በጉልበቱ ላይ ተደግፎ ወደ ሁለተኛው ረከዓ ይነሳል፡፡ ካልተመቸው ደግሞ በእጆቹ መሬት ላይ ተደግፎ ይነሳል፡፡ በመቀጠል ሱረት አል-ፋቲሓና የገራለትን ሱራ ይቀራል፡፡ በመጀመርያው ረከዓ ላይ ያደረገውን አይነት በዚኛውም ይደግማል፡፡

13 ሰላቱ ሁለት ረከዓ ብቻ ለምሳለ ሱብሒ፣ ጁሙዓና ዒድ አይነት ከሆነ ከሁለተኛ ሱጁድ ሲነሳ የቀኝ እግሩን ጣት ተክሎ



ግራ እግሩን ዘርግቶ ይቀመጥበታል፡፡ ቀኝ እጁን በቀኝ ጭኑ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ሁሉንም ጣቶቹን ጨብጦ በአመልካች ጣት ብቻ ተውሒድን ያመላክታል፡፡ የቀኝ እጁን ትንሿን ጣትና የቀለበት ጣቱን ጨብጦ አውራ ጣቱን ከመካከለኛው ጣት ጋር ቀለበት ብሰራና በአመልካች ጣቱ ብያመላክትም መልካም ነው፡፡ ሁለቱም ስርዓቶች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተገኝተዋልና፡፡ የሚመረጠው እነዚህን ቀያይሮ የተለያየ ጊዜ መስራት ነው፡፡ ግራ እጁን በግራ ጭኑና ጉልበቱ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ቀጥሎም በዚሁ አቀማመጥ ላይ እያለ ተሸሁድ (አት-ተሕያቱን) ይቀራል፡፡ እሱም የሚቀጥለው ነው፡-

التحيات لله، والصلوات، والطيبات، السلام عليك أيها النبي ورحمة الله وبركاته، السلام علينا وعلى عباد الله الصالحين، أشهد ألا إله إلا الله، وأشهد أن محمدا عبده ورسوله.

“አት-ተሒያቱ ሊልላሂ፥ ወስ-ሶለዋቱ ወጥ-ጠይዩባቱ፡፡ አስ-ሰላሙ ዐለይከ አይዩሃን- ነቢዩ ወረሕመቱልላሂ ወበረካቱሁ፡፡ አስ-ሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲልላሂ አስ-ሷሊሒን፡፡ አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለ-ልላሀ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ፡፡”

ትርጉሙም፡- ክብሮች ሁሉ የአላህ ናቸው፤ ፀሎቶችና መልካም ነገሮችም፡፡ አንተ ነቢይ ሆይ! ሰላም ባንተ ላይ ይሁን፤ የአላህ እዝነትና በረከቱም፡፡ ሰላም በኛና በደጋግ የአላህ ባሮች ላይ ይሁን፡፡ ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ እንደ ሌለ እመሰክራለዉ፤ ሙሐመድም የአላህ ባርያና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለዉ፡፡

ከዚህ በመቀጠል በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰለዋትና በረከትን ያወርዳል፡፡ እሱም የሚከተለው ነው፡-

اللهم صل على محمد، و على آل محمد، كما صليت على إبراهيم و على آل إبراهيم، إنك حميد مجيد، و بارك على محمد، و على آل محمد، كما باركت على إبراهيم، و على آل إبراهيم إنك حميد مجيد

ያአላህ ሆይ! በኢብራሂምና በቤተሰቦቹ ላይ እዝነትን እንዳወረድክ ሁሉ በሙሐመድና በቤተሰቦቹ ላይ እዝነትህን አዉርድ፡፡ አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡ በኢብራሂምና በቤተሰቦቹ ላይ በረከት እንዳወረድከው ሁሉ በሙሐመድና በቤተሰቦቹ ላይ በረከት አዉርድ፤ አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡ ከአራት ነገሮች እንዲህ በማለት በአላህ ይጠበቅ፡-

«اللهم إني أعوذ بك من عذاب جهنم ومن عذاب القبر ومن فتنة المحيا والممات ومن فتنة المسيح الدجال»

‹‹አላህ ሆይ! እኔ ከጀሀነም ቅጣት፣ ከቀብር ቅጣት፣ ከሕይወት ውስጥ እና ከሞት በኋላ ከሚከሰት ፈተና፣ እንዲሁም ከአል- መሲሕ አድ- ደጃል ክፉት ፈተና ባንተ እጠበቃለሁ፡፡››

ከዚያን ከዱንያና አኺራ ጥሩ ነገር አላህን ይለምናል፡፡ ለወላጆቹ ወይም ሌሎች ሙስሊሞች ዱዓእ ቢያደርግ ችግር የለውም፡፡ ሰላቱ ዋጅብ ወይም ሱና ልሆን ይችላል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኢብን መስዑድን ሲያስተምሩ የተናገሩት ቀጣዩ ንግግር ሁሉንም ያጠቃልላል፡- “ቀጥሎም የፈለገውን ዱዓእ መርጦ ያድርግ፡፡” በሌላ ዘገባ ደግሞ “ከልመና የፈለገውን ይምረጥ” አሉ፡፡ ይህ ደግሞ በአዱንያም ሆነ በአኺራ የሚጠቅመውን ሁሉ ያካትታል፡፡ ከዚያም በቀኙና በግራው “አሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላህ” (ሰላም በናንተ ላይ ይሁን! የአላህ እዝነትም) በማለት ያሰላምታል፡፡

14 ሰላቱ እንደ መግርብ ሶስት ረከዓ ወይም እንደ ዙህር፣ ዐስርና ዕሻእ አራት ከሆነ ያሳለፍነውን አት-ተሒያቱ ቀርቶ በሱ ላይ ሰለዋትን ይጨምራል፡፡ በመቀጠል "አላሁ አክበር" እያለ፣ እጆቹን እስከ ትከሻው ወይም ጆሮው ድረስ እያነሳ፣ በጉልበቱ ላይ ተደግፎ ይነሳል፡፡ እጆቹን እንደ በፊቱ በደረቱ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ፋቲሓን ብቻ ይቀራል፡፡ ዙህር ሰላት ውስጥ አንድ አንዴ በሶስተኛና አራተኛ ረከዓ ላይ ከፋቲሓ ሌላ ያለውን ብጨምር ችግር የለውም፡፡ ይህንን የሚያመላክት ነገር ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአቡ ሰዒድ ሐዲስ ዉስጥ ተረጋግጧልና፡፡ ከዚያን መግርብ ላይ በሶስተኛ ረከዓ፣ በዙህር፣ ዐስርና ዕሻእ አራተኛ ረከዓ ላይ ያሳለፍነውን አት-ተሒያቱ ቀርቶ ዱዓእም አድርጎ በቀኙና በግራው ያሰላምታል፡፡ ቀጥሎ ሶስት ጊዜ "አላህን ምህረት" ይጠይቃል (አስተግፍሩላህ) ይላል፡፡ በመቀጠል

"አልሏሁምመ አንተስ-ሰላሙ ወሚንከስ- ሰላሙ ተባረክተ ያ ዘ-ል-ጀላሊ ወል-ኢክራም" ይላል፡፡

ትርጉሙም:- "አላህ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ፡፡ የሰላም ምንጭም ነህ፡፡ የልዕልናና የልቅና ባለቤት የሆንከው አላህ ሆይ! ክብር ላንተ ይሁን፡፡"

ኢማም ከሆነ ወደ ሰዎች ሳይዞር ዚክሩን ይላል፡፡ ከዚያም የሚቀጥለውን ዚክር ያደርጋል:-

لا إله إلا الله وحده لا شريك له، له الملك وله الحمد وهو على كل شيء قدير، اللهم لا مانع لما أعطيت ولا معطي لما منعت ولا ينفع ذا الجد منك الجد، لا حول ولا قوة إلا بالله، لا إله إلا الله ولا نعبد إلا

إياه له النعمة وله الفضل وله الثناء الحسن لا إله إلا الله مخلصين له الدين ولو كره الكافرون

ላ ኢላሀ ኢልለልላህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ለሁ-ል-ሙልኩ ወለሁ-ል-ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር አልላሁምመ ላ ማኒዐ ሊማ አዕጠይተ፥ ወላ ሙዕጢየ ሊማ መነዕተ፥ ወላ የንፈዑ ዘል ጀድዲ ሚንከ-ል-ጀድዱ፡፡ ላሐውለ ወላቁወተ እላ ብላህ፣ ላ እላሀ እለላህ ወላነዕቡዱ እላ እያሁ፣ ለሁን-ንዕሙቱ ወለሁልፈድሉ ወለሁስ-ሰናእ አልሐስን፡፡ ላ እላሀ እለላሀ ሙኽልሲነ ለሁድ-ዲነ ወለው ከርሀል ካፊሩን፡፡

<u>ትርጉም፡-</u> ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም፤ እርሱ አንድ ነው አጋርም የለውም፡፡ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡ ንግስና የርሱ ነው፡፡ ምስጋናም ሁሉ ለርሱ ነው፡፡ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡ አላህ ሆይ! ለሰጠኸው ከልካይ፣ ለከለከልከው ሰጭ የለውም፡፡ ባለ ንብረትን ካንተ ቅጣት ንብረቱ ቅንጣት አይፈይደውም፡፡ ዘዴም ሆነ ኀይል ካንተ ዉጭ አይገኝም፡፡ ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም፡፡ ከእርሱ ሌላ ምንም ነገር አናመልክም፡፡ ፀጋም የርሱ ነው፡፡ ትሩፋትም የርሱ ነው፡፡ ጥሩ ዉዳሴም የርሱ ነው፡፡ ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም፡፡ ሙሽርኮች ብጠሉትም ኀይማኖትን ለርሱ ጥርት አድርገን (እንገዘዋለን)፡፡

33 ጊዜ አላህን ያጠራል (ሱብሐን አላህ ይላል)፣ 33 ጊዜ ያመሰግነዋል (አልሐምዱ ሊላህ ይላል)፣ 33 ጊዜ ያሊቀዋል (አላሁ አክበረ ይላል)፡፡ እነዚህ ዘጠና ዘጠኝ ይሆኑለታል፡፡ መቶ ለመሙላት ቀጣዩን ዚክር ይላል፡-

لا إله إلا الله وحده لا شريك له، له الملك وله الحمد وهو على كل شيء قدير

ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም፤ እርሱ አንድ ነው አጋርም የለውም፡፡ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡

ቀጥሎ ከሁሉም ዋጅብ ሰላት በኋላ ኣየት አልኩርሲይ፣ ሱረት አል-ኢኽላስ፣ ሱረት አልፈለቅና ሱረት አን-ናስ ይቀራል፡፡

ከሱብሒና መግሪብ ሰላት በኋላ የመጨረሻ ሶስቱን ሱራዎች ሦስት ጊዜ ቢደጋግም ይወደዳል፡፡ እነዚህ ሁሉ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተዘግበዋል፡፡ እነዚህ ዚክሮች ሱና ናቸው፣ ዋጅብ አይደሉም፡፡ ሁሉም ሙስሊም ሴትም ሆነ ወንድ ከዙህር ሰላት በፊት አራት ረከዓ፣ ከዙህር በኋላ ሁለት ረከዓ፣ ከመግርብ ሰላት በኋላ ሁለት ረከዓ፣ ከዕሻእ በኋላም ሁለት ረከዓና ከሱብሒ ሰላት በፊት ሁለት ረከዓ መስገድ ይችላል፡፡ አንድ ላይ አስራ ሁለት ረከዓ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ረከዓዎች “ራቲባ” ይባላሉ፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አገር ዉስጥ እያሉ አይተውዋቸውም ነበር፡፡ መንገድ ላይ ግን ከሱብሒ በፊት ያለው ሁለቱ ረከዓና ውትርን ብቻ ሰግደው ሌላውን ይተዋሉ፡፡ እነዚህን ግን አገርም ሆኑ ጉዞ ላይም እያሉ ይጠብቋቸዋል፡፡ በላጩ ውትርም ሆነ እነዚህን ራቲባዎች ቤትህ ዉስጥ መስገድህ ነው፡፡ መስጅድ ዉስጥ ቢሰግድም ችግር የለውም፡፡ ምክንቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- “ከግዴታ ሰላቶች ውጭ ለሰውየው በላጩ ሰላት ቤቱ ውስጥ የሚሰግደው ነው፡፡” እነዚህን ረከዓዎች መጠባበቅ ጀነት ለመግባት ምክንያት ይሆናል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- “በቀንና በሌሊት

አስራ ሁለት ረከዐዎችን ሱና የሰገደ በነርሱ ሰበብ አላህ ጀነት ውስጥ ቤት ይገነባለታል፡፡" ሙስሊም ሰሒሕ ኪታቡ ዉስጥ ዘግቦታል፡፡

ከዐስር በፊት አራት፣ ከመግርብ በፊት ሁለትና ከዒሻእ በፊትም ሁለት ረከዓ ብሰግድ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም ይህንን የሚያመላክት ሐዲስ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተዘግበዋልና፡፡

አላህ ሐቅን ይወፍቀን፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላም በነቢያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸዉ፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ ቅያማ ድረስ በጥሩ እነሱን በተከተለ ላይ ይስፈን!!!



IslamHouse.com

IslamHouseAM/ Bengali.IslamHouse islamhouse.com/am/

channel/UC0T_q-4JkqIMTfmxa1L3kTw

For more details visit
www.GuideToIslam.com

GUIDE TO ISLAM

contact us :Books@guidetoislam.com

GuidetoIslam.org Guidetoislam1 Guidetoislam www.Guidetoislam.com

المكتب التعاوني للدعوة وتوعية الجاليات بالربوة
هاتف: ٩٦٦١١٤٤٥٤٩٠٠+ فاكس: ٩٦٦١١٤٩٧٠١٢٦+ ص ب: ٢٩٤٦٥ الرياض: ١١٤٥٧

ISLAMIC PROPAGATION OFFICE IN RABWAH
P.O.BOX 29465 RIYADH 11457 TEL: +966 11 4454900 FAX: +966 11 4970126



# የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አሰጋገድ ስርዓት

ሶላትን በትክክል መስገድ በጣም አንገብጋቢ ጉዳይ ነው ይህ መጽሃፍ ስለ ነቢያችን ሶ/ዐ/ወ/ ሶላት ትምህርት በውስጡ ይዘዋል አንብበው ዕውቀት እንድቀስሙ ተስፋ እናደርጋለን።




IslamHouse.com
Osoul Center
www.osoulcenter.com